# አገር እንዴት ሰነበተች? ቁጥር 4     ጥር 28 ቀን 2014ዓም(05-02-2022)

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል እዬተዘጋጀ በተከታታይ በሚቀርበው አገር እንዴት ሰነበተች ?በተሰኘው  እርዕስ እንዳለፉት ጊዜያቶች የሰሞንኛውን የምንቃኝ ይሆናል።

መቼም መኖር ከተባለ ፣አገራችንም ከነብዙ ችግሯ እዬኖረች ከዛሬው እለት ላይ ደርሳለች።ያለፉት ቀናቶች ከራሞቷም ካለፉት የከፋና ይበልጥ ግራ የሚያጋባ እንጂ የተሻለ ነው አይባልም።ግራ የሚያጋባው ደግሞ ግራ የተጋባው መንግሥት ነኝ ባዩ የተረኞች ቡድን አገሪቱን ከድጡ ወደማጡ እዬከተታት ለነበረው ችግር መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ ሌላ ችግር እዬፈለፈለ መሄዱ እንዳለ ሆኖ በዬእለቱ የሚያስተላልፈው መልእክትና የሚሰጠው መግለጫ እርስ በርሱ የሚጋጭና የሚቃረን ሆኗል።የጠቅላይ ምኒስትሩ ንግግር ከውጭ ጉዳዩ ምኒስትሩ፣የውጭ ጉዳዩ ምኒስትሩ ከራሱ ቃል አቀባይ ባለስልጣን  መግለጫ ጋር የማይጣጣም መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል።ጠ/ሚኒስትሩ  ሰላም ለማውረድ ሲባል ከወያኔ ጋር ንግግር  ለማድረግ ፈቃደኛ ነው ሲል  የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከወያኔ ጋር ንግግር አይታሰብም ይላል።የራሱ ቃል አቀባይ መልሶ መንግሥታችን ለሰላም እጁን ይዘረጋል በሚል የገደምዳሚሾች የንግግር አዝማሚያውን ያበስረዋል። ሌላም ሌላም ነገር እንዲሁ።የወያኔው መሪ ደብረጽዮን በበኩሉ ውይይቱ መልካም ውጤት እያሳዬ ነው ማለቱም የተደበቀውን ሴራ ፈልቅቆ በማሳዬት ልማደኛውን ውሸታም ቡድን አጋልጦታል።የኦነጉ መሥራች ፣አሁን ብልጽግናን የወከለው የምክርቤቱ አባል የሆነውም ዲማ ነገዎ የውይይቱን መካሄድ አይቀሬነት ለቀረበለት የጋዜጠኛ ጥያቄ መልስ ሰጥቷል።

ይህ በእንዲህ እያለ  ወያኔ የድርድር አቅሙን በማጎልበት ላይ ይገኛል።የትግራይን ሕዝብ በውድም በግድም ለከፈተው ጦርነት እንዲሰለፍ ግዳጅ አውጥቶ እዬመለመለውና  በተለያዩ የጦር ግንባሮች እያሰለፈው ነው። አሁንም የአማራውንና የአፋሩን መሬት በጉልበት ይዞ ፣ያልያዘውን አካባቢ ለመያዝ ያለ የሌለ ሃይሉን አሰባስቦ በማጥቃት ላይ ይገኛል።ሥልጣን ላይ ያለው የኦሮሙማው ቡድን የወያኔን የጥቃት እርምጃ በበጎ ያዬው  ይመስላል፤ ለይስሙላ ከማላዘን ባለፈ የሚጠበቅበትን የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታውን አልተወጣም።የወሎን  መሬት ለመከፋፈል ምሥጢራዊ ስምምነት የገቡ ይመስል ሰሜን ወሎ በትግራይ ወያኔ ወራሪ መወረሩን ተቀብሎ  በማጽደቅ  ደረጃ ትንፍሽ አይልም። የኦነግ መራሹ ኦሮሙማው ቡድን የደቡብ ወሎን  የመሰልቀጥ ፍላጎት ሕጋዊ የሚያደርግበት ውል አድርጎ ቆጥሮታል።ኦነግ መራሹ ኦሕዴድ የወልቃይትና ጠገሌም ለም መሬት በወያኔ ትግሬ ወራሪ ሃይል ቢወሰድ ደንታ የለውም ፤ የተቸገረው ቆራጡ የጎንደር ሕዝብ የማይቻልና የማይበገር ሆኖበት እንጂ ቢዳከም ለወያኔ ባለቤትነቱን ባበሰረለት ነበር።እንኳንስ የወልቃይት መሬት የኢትዮጵያን ድንበር አልፋ ሱዳን ለያዘችው መሬት መች ተጨነቀ?ያም ደንታ ቢስነቱን ያረጋግጣል።

የአፋርም ቢሆን በወያኔ ወራሪ ተደጋጋሚ ጥቃት እዬተሰነዘረበት፣በከባድ መሣሪያ ከያቅጣጫው ሲደበደብ፣ ብዙ ሕዝብ ተገሎና ተፈናቅሎ፣ ንብረት ወድሞ የመንግሥት ያለህ ሲባል በሥልጣን ላይ ያለው ጉደኛው ቡድን መከራውን እራስህ ተወጣው ብሎ ዕዳውን ለአፋር ሕዝብ ትቶታል።ለጥሪውና ለጩኸቱ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎታል።የአፋር ሕዝብ ከራሱ መሬት በላይ ለጠንካራው ኢትዮጵያዊነቱ ፣ ለሚያውለበልበው አረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ሰንደቁ የሚከፍለው ዋጋ  ሆኗል።በወሎና በአፋር ሕዝብ ላይ የወያኔ ወረራ ለኦነግ ኦሕዴዳውያን ኢትዮጵያን ተቀራምቶ የማፍረስ የጋራ ፍላጎት መንደርደሪያ ተደርጎ ተወስዷል።

አሁን አሁንማ ወያኔን ጁንታ የሚለውም ሆነ በፓርላማ አሸባሪ በመባል የጸደቀ ስያሜ ከመንግሥትና ከተከታዮቹ አንደበት እዬጠፋ ወንበዴ በሚለው የተራ ሽፍታ ስያሜ ተተክቷል።አገር ለማፍረስ የተነሳ መሆኑ ሲታወቅ በዚህ አይነቱ ዝቅተኛ ደረጃ መመደቡ የዓላማ አንድነት ለመኖሩ ማሳያ ነው።እርቅና ሰላም በሚል ጨዋታ ወያኔም ሆነ ግብረ አበሩ የኦነግ አሸባሪ ቡድንም የፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀሉ በተራ ደረጃ እንዲታይለትና ሁሉም በእርቅና ሰላም ውይይቱ ጠረጴዛ ላይ እንዲቀመጥ ለማድረግ የተሸረበው ተንኮል በመውጣት ላይ ነው። ለቅድመ ውይይቱም በዬጎረቤት አገራቱ የሚስጥር ግንኙነት በመካሄድ ላይ መሆኑ ብዙ እዬተወራ ፣ፍንጭም እዬወጣ ነው። በግልጽም የሰሞኑ የአብይ አህመድ ኢሚሬት መሄድ፣የባለሥልጣናቱ ሳውዲ መግባት፣በኬንያም በኦሕዴድ በኩል የለማ መገርሳና የወርቅነህ ገበዬሁ፣በህወሃት በኩል ,ነሰዬ አብርሃና የነብርሃነ ገ//ክርስቶስ ገባ ወጣ ማለት ሹክሹክታ ለእረፍት እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተገንዝቦታል።የኬንያው መሪ ኡሁሩ ኬንያታም ወደ አዲስ አበባ መመላለስ በየፓርኩ ለመዝናናት አይደለም፤ እሱም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ ጉተሬዝ ሰላም ሰላም የሚሉት የተቀናጀ ጫጫታ ያለምክንያት አይደለም። በስከጀርባ የሚሠራውን ደባ የሚያሳይ ነው። ጉተሬዝማ የቤጅንን የክረምቱን ኦሎምፒክስ ጨዋታ የመማጸኛ ጣእት በማድረግ ዓለም አቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙትን ሃይሎች የሰላም አካል ተደርገው እንዲቆጠሩና በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲቀመጡ ተማጽኗል።እንዲህ ነው የዓለም አቀፍ ፍትሕና ሕግ መከበር ማለት። ከስድስት ወራት በፊት በጃፓን ከተማ በቶኪዮ የተካሄደው የኦሎምፒክስ ጨዋታ ግን ለተማጽኖ አልቀረበም ነበር፣ምክንያቱም በዛው ሰሞን ወያኔ እዬወረረ በመምጣቱ ጉተሬዝ የሚመራውን ተቋም የሚያሽከረክሩት በአሜሪካ የሚነዱት ምዕራባውያን ያሸንፋል የሚል እምነትና ምኞት ስለነበራቸው ነው።አሁን ግን የጠበቁት ስላልተሳካ የኦሎምፒክስ ጨዋታውን የሰላም ካርታ አድርገው ብቅ ብለዋል። በኢትዮጵያ ፍትሕ ይከበር ከተባለ ወያኔና ኦነግ መራሹ አሸባሪ ሃይልና በመንግሥት ውስጥ ያሉት የኦሕዴድ መራሹ የብልጽግና ባለሥልጣናት ተባባሪዎች ለፍርድ ቀርበው ለፈጸሙት ጥፋት ተመጣጣኝ ቅጣታቸውን ሲያገኙ ብቻ ነው። ለዋና ጸሓፊ ጉተሬዝ የምንለው ቢኖር አዎ የኦሎፒክስ መንፈስ ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር ነው፤ታዲያ እርሰዎ ይህንን ያወቁት በአሁኑ የክረምቱ ኦሎምፒክስ ጊዜ መሆኑ አሳዝኖናል፣እርስዎንም እንድንታዘብዎት አድርጎናል።ለመሆኑ ባለፉት ኦሎምፒክስ ጨዋታዎች የት ነበሩ?ወይስ በዓለም ዙሪያ ሰላም ሰፍኖ ነበር?እርግጥ ነው የኦሎምፒክስ መንፈስ ዘረኝነትን፣ መለያዬትን፣ግጭትን ይኮንናል፤በሰው ልጆች መካከል ሰላምና ፍቅር እንዲኖር፣አገራት ከግጭትና ከጦርነት እንዲርቁና በሰላም እንዲኖሩ ያሳስባል፣ይህ ማለት ግን ወንጀለኞችና ለተጠቀሱት መልካም መልእክቶች ጸር የሆኑትን አቅፋችሁ ደግፋችሁ ኑሩ የሚል መልእክት የለውም።ያንን የሚያራምዱ የኦሎምፒክስ መንፈስ ተቃራኒና ጠላቶች ብቻ ናቸው።ወንጀልን ለማጥፋት ወንጀለኛን ማጥፋት ተገቢና አስፈላጊ ነው።ጦርነትን ለማሶገድና ሰላምን ለማስፈን፣ጦረኛን ማሶገድ፣ በዘረኝነት የሚነሳ ግጭትን ለማሶገድም በዘርና በጎሳ ከፋፍሎ የሚያጫርስን አረመኔ ሥርዓትም ሆነ ቡድን ማሶገድ የግድ ይላል። ታሪክ እንደሚመሰክረው ጀርመንም ሆነች ሌሎቹ የአውሮፓ አገሮች የተገነቡት በናዚዎች መቃብር ላይ ነው።ኢትዮጵያም ልትገነባ የምትችለው በዘረኞችና በጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች መቃብር ላይ ይሆናል።

ሌላው የሰሞኑ አነጋጋሪ ጉዳይ ኢትዮጵያን የግል ንብረቱ ያደረገው የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን መሪ አብይ አህመድ በውጭ አገር የሚያደርገው ጉብኝት፣ግንኙነት፣የሚፈርመው ውል፣የሚገኘው ብድርና እርዳታ ምን እንደሆነ ሳይታውቅ እንደተለመደው ተሸፋፍኖ መቅረቱ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ የማወቅ መብቱ ከተነፈገው ውሎ አድሯል።ይህንንም ደፍሮ የሚጠይቅ ተቃዋሚ ነኝ ባይ የፖለቲካ ድርጅት የለም።ከሚገኘው እንጥብጣቢ ቢደርሰኝ በሚል ጉጉት ውስጥ ያለ እስከሚመስል ድረስ ድምጹን አጥፍቶ ተቀምጧል።አሁንም መንግሥት በሕዝብና በአገር ስም የሚያደርገውን ግንኙነት፣ውልና ስምምነት ይፋ ያድርግ፣ ሕዝቡ ማወቅ አለበት እንላለን።ገና የግንባታው ሥራ ሳይጠናቀቅ ከሕዳሴ ግድቡ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ሃይል ለጎረቤት አገራት መሸጡ ተሰምቷል።ያ በብርሃን ይምነሽነሻል

የተባለው የገጠሩ ቀርቶ የከተማው ሕዝብ ዛሬም በጨለማ ውስጥ እዬዳከረ፣በራሽኝ እዬተዳረሰ ነው። ኤሌክትሪኩ መሸጡ እንጂ ለማን በስንት፣እንደሆነ ይፋ አልሆነም፤ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ነው። የወርቅና የሌላው ማዕድን፣የፍራፍሬው፤የአበባው፣የቡናው፣የቆዳና ሌጦው---ወዘተ ሽያጭና የት እንደገባም የሰማይ ቤት ምስጢር ሆኗል።ይህ በእንዲህ እያለ፣

የኦሕድድ መራሹ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ሕዝቡን የማለያዬቱን ሴራ ቀጥሎበታል።ከሰሞኑም የደቡብ ክልል ፕሬዚደንት ተብዬው እርስቱ ይርዳው የተባለ ከፋፋይ ጠብደል በአሜሪካን አገር በኢትዮጵያ ኤምባሲ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የጉራጌ ማህበረሰብ የሆኑትን ብቻ ለይቶ በመጥራት ለዘመናት የያዙትን ኢትዮጵያዊነት ማንነታቸውን አውልቀው ለጠባብ ጎሰኝነት ማንነት እንዲቆሙ በሚስጥር ቅስቀሳ ማድረጉን በቪድዮ ተቀርጾ የወጣው ማስረጃ አጋልጦታል።እንደሰውዬው አባባል የጉራጌ ማህበረሰብ ሥልጣን ከወጣው ጋር አጫፋሪና አሽከር ሆኖ ቢኖር ይጠቅመዋል የሚል ወራዳ መልእክት ይዞ የመጣ አድር ባይ መሆኑን በግላጭ አሳይቷል።በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን እኩልነት ሳይሆን በአሽከርነት የሚወረወርለትን ተቀብሎ ቢያድር ለጉራጌ ማህበረሰብ በቂው ነው ባይ ነው። አቶ እርስቱ በዚህ የደላላ ሥራው የያዘው ወንበሩን ለማጠናከር እንጂ ለጉራጌው ማህበረሰብ አስቦ እንዳልሆነ በማህበረሰቡ ላይ የሚደርሰውን ተደጋጋሚ ጥቃት አንድም ቀን ቢሆን ሲቃወም ተሰምቶ አለመታወቁ ለማህበረሰቡ የሚዘነጋ አይደለም።ይህንን ቀናና አገር ወዳድ፣ታታሪ ሕዝብ ከታሪካዊ አጋሩና ቤተሰቡ ከሆነው ከሌላው ኢትዮጵያዊ በተለይም ከአማራው ማህበረሰብ ነጥሎ የጅቡ የኦሮሙማው ምሳና እራት ለማድረግና በኦነግ መረብ ለማጥመድ የሞከረው እርስቱ ይርዳው ቀደም ሲልም ይህንን ማህበረሰብ ካስጠቁት መካከል አንዱ ነበር። አሁንም በሥልጣን ላይ ተቀምጦ እያስጠቃው ይገኛል።የዛሬው ሙከራው ግን ከሌላው ጊዜ ሁሉ የተለየና የከፋ፣ የጉራጌውን ማህበረሰብ ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው። ህዝቡንም የናቀ ድፍረት ነው።ይህንን ኩሩ ጨዋ ሕዝብ እንደ እራሱ ባርያና አጃቢ ለማድረግ መድፈሩ ብቻ ከሥልጣን ወንበሩ እንዲወገድ ያደርገዋል።በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው፣ የኦነግ ኦሕዴድን ሴራ የተገነዘበው የጉራጌ ማህበረሰብ ተወላጅ ሁሉ ይህንን የጥፋት መላክተኛ አትወክለኝም ከሥልጣን ወንበር ውረድ ሊለው ይገባል።ኦነግ ኦሕዴድ በአዲስ አበባ ላይ ላለው የይገባኛል የመዋጥ ጥያቄ ኢጋዥና ተባባሪ ይሆነኛል ከሚል ህሳቤ የመነጨ ፣አማራውን ነጥሎ ለመምታት የታቀደ ሴራ መሆኑን አገር ወዳዱ የጉራጌ ማህበረሰብ ይረዳዋል ብለን እናምናለን።አማራው ሲመታ ሌላው ይቀርለታል ማለት አይደለም።የጉራጌ ማህበረሰብ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን የሚኖርበትም የገጠር አካባቢ በቀጣይ በኦሮሙማው ሰልቃጭ ቡድን ሊዋጥ እንደሚችል ከወዲሁ ሊገነዘብና የስርዓቱን ተላላኪ እርስቱ ይርዳውን ወግድ፣ውረድ ከጫንቃዬ ሊለው ይገባል እንላለን። በዚህ ወራዳ ቅስቀሳ የተማረኩ ጥቂት እበላ ባዮች መኖራቸው አይካድም።ለነዚህ እንኳንስ አገር የወለዱትንም ልጅ ቢሆን ሸጠው ከመብላት የማይመለሱ አረመኔዎች ናቸው። እነዚህ ዳግመኛ ይሁዳዎች የጃቸውን ግን ማግኘታቸው አይቀርም።በከባቢያቸው የሚኖረው አገር ወዳድ ፊት ሊነሳቸው ይገባል።

የተረኛው ኦሕዴድ ኦነግ ሌላው በቀጣይነት የታዬው የሰሞኑ ድፍረት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በአማኙ ላይ በከንቲባዋ በአባዳነች አቤቤ በኩል ያሳዬው ንቀት ነው።እንደሚታወቀው ባለፈው አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ የአብይ አህመድ የኦሮሙማው መንግሥት በጥምቀት በዓሉ አከባበር ዙሪያ ያደረገው ድፍረትና የንጹሃን ደም ማፍሰስ ሳይበቃው ፣ከጥፋቱ ይታረማል ተብሎ በአንዳንድ የዋህ አማኞችና የእምነት አባቶች ሲጠበቅ ጭራሽ ከለዬለት ድፍረት ውስጥ የገባበትን በታሪክ ያልታዬ ማን አህሎኝነት የታዘብንበት ወቅት ነው።በመስቀል አደባባይ የይገባኛል ጥያቄ ምክንያት ሲኖዶሱ በቤተክህነቱ መንበር ከከንቲባዋ ጋር ተገናኝቶ ለመወያዬት ያደረገላትን ጥሪ ከተራ የቀበሌ መሪዎች እንደቀረበ በመቁጠር አዲስ ሸራተን ሆቴል ድረስ መጥታችሁ እንገናኝ እንጂ እኔ ሲኖዶሱ መንበር ድረስ

አልመጣም በማለት የታቀደው ንግግር እንዳይካሄድ አድርጋለች።እንደብልግናዋማ ከሆነ ከአምስት ኪሎ ወረድ ብላችሁ አራት ኪሎ በሚገኘው ቱሪስት ሆቴል እንገናኝ አለማለቷም ከተማውን ካለማወቋ እንጂ እንደድፍረቷማ ቢሆን ቡራዩ ወይም እንጦጦ ፓርክ  ድረስ ኑ ብትል አያስደንቅም።ጥያቄውን አለማክበሯ፣ አባቶችን የሆቴል ቤት ደንበኞችና ተሰብሳቢ አድርጋ ማዋረዷ  በቤተክህነቱና በምእመናኑ ትልቅ ቁጣን የቀሰቀሰ ሲሆን የኦሕዴድ-ብልጽግና  ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶነትን በጉልህ አሳይቷል። ለበለጠ ቀውስም መነሾ ምክንያት ይሆናል።በማንም ያልተደፈረው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ በዚህ ደረጃ ሲዋረድ ዝም ይላል ብለን አናምንም።ዝም ካለም ለውድቀቱና ለድፍረቱ እራሱ ተጠያቂ ነው እንላለን።ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ነውና አባቶች አላፊነታቸውን በመወጣት የቆሙለትን እምነትና የሚከተላቸውን ምእመናን አክብረው ሊያስከብሩ ይገባል።በውስጣቸው ያሉትንም ሰርጎ ገቦች በማሶገድ ቤተክርስቲያኗን  ንጽህናዋንና ክብሯን አስጠብቀው ሊታደጓት ይገባል እንላለን። ለዳግመኛ ጊዜም በዪካቲት ውስጥ ለማነጋገር ጥሪ ለማድረግ የወሰኑ ሲሆን የሚያገኙትን መልስ የምንሰማው ይሆናል።

ወደሌላው ሰሞንኛው ጉዳይ ስንመለስ

በጀፍሪ ፌልትማን ቦታ የተተካው የአሜሪካኖቹ መልእክተኛ የሆነው ጀፍ ፒርስ(jeff pierce) ኢትዮጵያ ገብቶ ያዪውንና የታዘበውን ይፋ አድርጓል።ባወጣው መግለጫ ወያኔ በወሎ በተለይም በደሴና ኮምቦልቻ እንዲሁም  በአፋር ያደረሰውን ጉዳት፣ግድያ፣ዘረፋና ውድመት በሚመለከት አድራጎቱን የኮነነና የሰው ልጅ ይፈጽመዋል ብሎ ከሚገምተው በላይ እንደሆነበት የገለጸ ሲሆን አነግና መሰሎቹ በሌሎቹ ቦታዎች በተለይም በኦሮሞ ክልልና በቤኒሻንጉል ውስጥ የፈጸሙትን ወንጀል ግን ሳይጠቅስ አልፎታል። በእኛ ግንዛቤ ይህንን ያደረገው በሥልጣን ላይ ያሉት ተረኞቹ እጃቸው ስላለበት ከነሱ ጋር ላለመቀያዬም ሲል ነው ብለን እናስባለን። ሰውዬው ለረጅም ዓመት በዲፕሎማሲው መስክ ላይ የቆዬ ከመሆኑ አንጻር ስለኢትዮጵያና ስለሕዝቧ ያሰማው አወታዊ ቃል የሚጠበቅ ነው።እንደሌሎቹ በጉልበት አገኛለሁ በሚል እብሪታዊ አካሄድ ካደረሱት ውድቀት የተማረና ለጊዜውም ቢሆን የተላቀቀ ይመስላል።መጨረሻውን የምናዬው ይሆናል።መቼም ቢሆን አሜሪካኖች ለጥቅማቸው ሲሉ አንዴም ቄስ ሌላም ጊዜ ሰይጣን የመሆን ድርብ ድርብርብ ጸባይ አላቸውና ማመን ያስቸግራል።የኦሕዴድ መራሹ ቡድን ካደረገው መልመጥመጥና እጅ መስጠት ጋር የተያያዘ መለሳለስም ሊሆን ይችላል ብለን እናምናለን።

በሰላምና እርቅ ኮሚቴው ዙሪያ ያለው እንቅስቃሴም የሰሞኑ ትኩረታችን ነው።የተቋቋመው ኮሚቴ በሕዝቡ የተመረጡ ሰዎች የተካተቱበት ባለመሆኑ የሕዝቡን ሙሉ አመኔታ ያገኘ አይመስልም። አብዛኛዎቹ በወያኔ ጊዜ ስልጣን ላይ የነበሩና አሁንም በኦሕዴድ መራሹ መንግሥት ጋር በተለያዩ ዘርፎች ግንኙነት ያላቸው፣ወይም ላለው ስርዓት እውቅና የሚሰጡ ሰዎች ናቸው። የችግሩ መነሻ ምን እንደሆነ ፣የመረጣቸው አካል፣የተመረጡበት መለኪያ፣ሊተገብሩ የታሰበው ዓላማ፣እነማንን ለማናገርና ለማወያዬትም እንዳቀዱና መስፈርታቸው ምን እንደሆነ፣ውይይቱ በምን ነጥቦች ላይ እንደሚያተኩር፣ በኢትዮጵያ አንድነት፣በአወዛጋቢው ሕገመንግሥት፣በአገራዊ አወቃቀር፣በሰንደቅ ዓላማ ላይ እራሱ ኮሚቴው ምን አቋም ይዞ እንደሚንቀሳቀስ አይታወቅም፤ ግልጽ አይደለም።ለጦርነቱ መነሻ ምን እንደሆነ፣ የደረሰው ውድመትና ጥፋት መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ማጥናቱ አይታወቅም። ለደረሰው ጉዳት ማን ተጠያቂ እንደሆነም ኮሚቴው የያዘው አቋም ይህ ነው አልተባለም። ጥፋተኛውን የሚቀጣበት ፣የተጎዳው የሚካስበት አቅምና ሥልጣኑ እስከምን ድረስ እንደሆነም አልተብራራም። የኮሚቴው አባላት በዚህ አይነቱ ተሳትፎ ልምድና እውቀት ያላቸው መሆኑም አጠያያቂ ነው። መንግሥት የምፈልገውን ያደርጉልኛል ከሚል ፍላጎቱ ሰብስቦ የሰየማቸው ባሕላዊ ያገር ሽማግሌዎች

ናቸው የሚለው ትችት ያስተጋባ ሲሆን የእኛም ትችት ከዚያ የራቀ አይደለም። ወጣም ወረደም ያገሪቱን ችግር መፈተሽና ተጠያቂውን አካል ለይቶ ማውጣት፣ተመሳሳይ ችግርም እንዳይከሰት የሚከላከሉበት ዘዴ መፈጠር እንዳለበት እናምናለን።ለዚያም ውይይትና የእርቁ ሂደት ከፍትሕ ሚዛን የራቀ መሆን የለበትም እንላለን።አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ጉንጭ አሳስሞ የሚለያዩበት እንዳይሆን ሕዝቡና የሕግ ባለሙያዎች በንቃት ሊከታተሉት ይገባል።ጥፋተኛ ሳይቀጣ ከታለፈ ጥፋት በጥፋት ላይ እንዲጨምርና ባሕል ሆኖ እንዲቀር ያደርጋል። ትውልድ ሊማርበትም አይችልም።ፈጣሪ እንኳን በእጁ የፈጠረውን የሰው ዘር ለጥፋቱ ሞትን አስቀምጦለታል።ሁሉም እንደሚያምነው የችግራችን ምንጭ የሆነው የጎሳ ፖለቲካና ፣ያንን የሚንከባከበው በሕገመንግሥት ስም የሰፈነው አገር አፍራሽ፣ሕዝብ አጫራሽ የሆነው መመሪያ ሰነድ ነው።ያንንም ተከትሎ የተዘረጋው ክልላዊ አስተዳደርና የዚያ ጥምረት የሆነው ፌዴራሊዝም ነው።

የውይይቱ ጭብጥና መደምደሚያ ጥፋቱን ንጉሡ አጥፍቷል፣ግን ገበሬው ይካስ እንዳይሆን እንሰጋለን። ወንጀለኞቹ ተለቀው ተመስግነውና ተሸልመው ጉዳተኞች ተወቅሰውና ተኮንነው፣ብሎም ታፍነው የሚኖሩበት አገር ዱሮም ሆነ በቅርቡ ያዬነው ጉድ ነው።

ይኖራል ይኖራል ይህም ኑሮ ሆኖ፣

ያለማው ሲወቀስ አጥፊው ተመስግኖ።

የተገላቢጦሽ ሆነና ነገሩ፣

ተከሳሾች ነጻ ከሳሾች ታሰሩ።

አገር የበደለው ጎሽ በርታ ሲባል፣

ላገሩ የሠራው እስር ቤት ይገባል።

መንግሥት ተብብዬው የኦሮሙማው ቡድን ተቃዋሚዎቹን እያሳደደ፤እያሰረና እያሸበረ መሄዱን ቀጥሎበታል።በፋኖ ላይ የከፈተው ዘመቻ አሁንም ተጠናከረ እንጂ አልቀነሰም።በእውነት ተናጋሪ ጋዜጠኞችና የመብት ተከራካሪዎች ላይም ወከባው እዬጨመረ ሄዷል።የኦሮሞ ተወላጅ ሆነው፣ካለው የኦሮሙማ አገር አጥፊና አክራሪ ቡድን ጋር ግብግብ የገጠሙት ፣በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩትም የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል።ታምራት ነገራ፣ አስቴር በዳኔና ፓስተር ቢኒያም ለዚያ ማሳያዎች ናቸው።የጎሳ ማንነታቸው ወይም የእምነት አጋርነታቸው አላዳናቸውም።በዚህ መልክ የታሠሩ ብዙዎች ናቸው።

የሕዝቡን እይታና ትኩረት ለማስለወጥ የድርቅና የችግሩን ወሬ በፊልም በመቅረጽ እንደለመደው ገንዘብ ለመሰብሰብ፣በእርዳታው የመጠቀም ልማድ ያላቸውን የመንግሥቱ ተባባሪ የሆኑ ልክስክስ ግለሰቦችን አሰልፏል።ለችግረኞቹ መርዳት ተገቢ መሆኑን የምናምንበት ሲሆን በነዚህ የእርዳታ ገቢ በመቦጨቅ በሚተዳደሩ ጬልሌዎች በኩል የሚገባው ለችግረኞቹ እንደማይደርስ፣ቢደርስም ተመናምኖ መሆኑን ካለፈው ድርጊታቸው ስለምናውቅ፣የእርዳታው ማስተባበሩ ሥራ በችግሩ ሰለባዎች ዙሪያ ባሉት በኩል እንዲሆን ለማሳሰብ እንወዳለን። ከአሜሪካና ከአውሮፓ ለእርዳታ የተሰበሰበ ብዙ ገንዘብ የት እንደገባም ባለመታወቁ እያነጋገረ ነው።እርዳታ አድራጊው ጥንቃቄ እንዲያደርግ ምክራችን ነው።

የዛሬውን አገር እንዴት ሰነበተች መልእክታችንን በዚህ እናጠቃልላለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ፋኖ የአገር ክብር ዘበኛ፣ የሕዝብ እምባ ጠባቂ ነው!!ሁሉም ፋኖ ይሁን!!